# አዋጅ ቁጥር ______/2018

## የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በአየር ትራንስፖርት ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ላይ እየጨመረ የመጣውን ተለዋዋጭ የደህንነት ስጋት በብቃት ለመከላከል የአለም አቀፍ የሲቪል አቬዬሽን ድርጅት ያወጣውን የተቀጽላ 17 አስገዳጅ ስታንዳርዶችን ለማካተት፤ የአቬዬሽን ሴኩሪቲ ዘርፍ አቅም በቴክኖሎጂ ለማዘመን እና ተጨማሪ ስልጣንና ተግባር መደንገግ በማስፈለጉ የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አዋጅ ቁጥር 432/1997 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር__/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አዋጅ ቁጥር 432/1997 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤

1/ የአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4)፤(7)፤እና (10) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4)፤(7)፤እና (10) ተተክተዋል፤

"4/ **"አደገኛ ቁሳቁስ"** ማለት በአውሮፕላኑ የመንገደኞች ክፍልም ሆነ በጭነት ማስቀመጫ ውስጥ ቢጫን የመንገደኞች ጤንነት፣ ደህንነት፣ ንብረት ወይም አከባቢ እንዲሁም የአውሮፕላኑን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥል ማንኛውም ዓይነት ቁሳቁስ ወይም ንጥረ ነገር ነው፤

"7/ **"ፍተሻ"** ማለት ሕገ-ወጥ የጣልቃ ገብነት ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ ፈንጂዎች ወይም ሌሎች አደገኛ ቁሳቁሶችን ቴክኒካዊ በሆነ ወይም በሌላ መንገድ ለይቶ ለማውጣትና ለማስቀረት የሚደረግ የሴኩዩሪቲ ቁጥጥር ነው፤

"10/ **"ለደህንነት የተከለከሉ ስፍራዎች"** ማለት ለከፍተኛ ስጋት ተጋላጭ መሆናቸው የተለዩ በጥብቅ የተከለከሉ ወይም የሚጠበቁ እንዲሁም ተጨማሪ የደህንነት መቆጣጠሪያ ተግባራት የሚከናወንባቸው በኤርፖርት ውስጥ የሚገኙ ስፍራዎች ናቸው፤

2/ “አግባብ ባላቸው ህጎች በተደረገው የስያሜ ለውጥ መሰረት በአዋጁ ከተጠቀሱ ባለድርሻ አካላት የደህንነት፣ኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን የሚል ስያሜ ወደ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፤የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኢንተርፕራይዝ ወደ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ስያሜ ለውጥ ተደርጓል”

3/ የአዋጁ አንቀጽ (3) ርዕስ እና ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ርዕስ እና ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፤

“3. <u>የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት</u>

1/ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ በተቋቋመበት ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ስራዎችን በበላይነት ለማስፈፀም አግባብነት ያለው ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።”

4/ “ከአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ዐ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ዘ)፣ (ዠ)፣ (የ)፣(ደ)፣(ጀ) እና (ገ) ተጨምረዋል፤”

“ዘ) የአየር መንገድ ኦፕሬተሮች፣ የአየር ትራፊክ አገልግሎት ሰጪና የሌሎች ተቋማት የሴክዩሪቲ ፕሮግራምና መመሪያ ከዚህ አዋጅ አንፃር ይገመግማል፤ ያፀድቃል፤

ዠ) በአይሮፕላንና በአይሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች ላይ ሕገ-ወጥ ጣልቃ ገብነት ሊፈፀምባቸው የሚችሉ ከትከሻ የሚተኮስ የአየር መከላከያ መሳሪያ ወይም ስጋት ማድረስ የሚችል ማንኛውም ነገር ወይም ሰው አልባ አውሮፕላን ዝውውር ቁጥጥር ያደርጋል፤ሊቃጣ የሚችል አደጋን ለመከላከል ስርዓት ይዘረጋል፤እርምጃ ይወስዳል፤

የ) “ወደ ኢትዮጵያ የሚበሩ ኦፕሬተሮች የበረራ ደህንነት ኦፊሰር ስምሪት ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤”

ደ) ከአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተቀጽላ 17 እና ከሌሎች ሕጎች ጋር የተጣጣመ የተዛፈ ብሔራዊ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ተግባራዊ ያደርጋል፤”

ጀ) ብሔራዊ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ጥራት ቁጥጥር የስራ ክፍል ያቋቁማል፤ ያለገደብ በማንኛውም ቦታ በመንቀሳቀስ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ

ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና መስፈርቶች አተገባበር ተገቢነት ያረጋግጣል፤ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤"

ገ) የመንገደኞችን ምዝገባ እና ቅድመ-በረራ መረጃ የመሰብሰብና የማሰራጨት ትግበራን ይመራል፤ያስተባብራል።"

5/ የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተሰርዟል።

6/ የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፤

"3/ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኪዩሪቲ የስልጠና ፕሮግራም ይዘትንና የማሰልጠኛ ተቋማት የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስለስልጠና ያወጣቸውን ደረጃዎችና ተመራጭ ሀሳቦችን የጠበቁ ስለመሆናቸው ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አግልግሎት ጋር በጋራ ያረጋግጣል"

7/ "ከአዋጁ አንቀፅ 7 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀፆች 8፣9፣10፣ እና 11 ተጨምረዉ ከአንቀጽ 8 እስከ 21 የተቀመጡ ነባር ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸዉ ከአንቀፅ 12 እስከ 25 ሆነዉ ተሸጋሽገዋል፤"

"8. <u>የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባርራት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፦

1/ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ አካላት የሳይበር ደህንነት ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ድጋፍ ያደርጋል፤

2/ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨባጭ የሆነ የሳይበር ደህንነት ስጋት መኖሩ ሲረጋገጥ የጥንቃቄ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

3/ በየኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል።

9. <u>የኢትዮጵያ አርቴፍሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባርራት እንደተጠበቀ ሆኖ የአርቴፍሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት፦

1/ የአቪዬሽን ደህንነት ለመጠበቅ ስራ ላይ የሚውሉ የአርቲፊሻ ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂዎችን በማዘመን ረገድ ድጋፍ ያደርጋል፤

2/ የአቪዬሽን ደህንነት ተግባራት በጥራት፣ በቅልጥፍናና በብቃት

እንዲፈፀሙ ድጋፍ ያደርጋል፤

3/ በኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል።

10. <u>የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፦

1/ የኢሚግሬሽን ቁጥጥር የሚከናወንባቸውን የኤርፖርት ኢሚግሬሽን ኬላዎችና ስፍራዎች ይቆጣጠራል፤

2/ ለኤርፖርቱና ለአየር ትራንስፖርት ስርዓት ደህንነት ስጋት በሆኑ ጉዳዮች ላይ መረጃ ይለዋወጣል፤

3/ በየኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል።

11. <u>የጉምሩክ ኮሚሽን</u>

በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የጉምሩክ ኮሚሽን፦

1/ የጉምሩክ ቁጥጥር የሚከናወንባቸው የኤርፖርት ጉምሩክ ስፍራዎችን ይቆጣጠራል፤

2/ ለኤርፖርቱና ለአየር ትራንስፖርት ስርዓት ደህንነት ስጋት በሆኑ ጉዳዮች ላይ መረጃ ይለዋወጣል፤

3/ በኤርፖርቶች ደረጃ በሚቋቋሙት የሴኪዩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል፡፡"

8/ "ከአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (6) እንደተሻጋሽገ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ሸ)፣ (ቀ)፣ (በ) እና (ተ) ተጨምረዋል፤"

"(ሸ) የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር -------------------------አባል፤

"(ቀ) የኢትዮጵያ አርቴፍሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት -----------------አባል፤

"(በ) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ------------------------------ -አባል፤

"(ተ) የጉምሩክ ኮሚሽን ------------------ -----------------------------አባል፡፡"

9/ "ከአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (6) እንደተሻጋሽገ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፤"

“3/ በኢትዮጵያ በኩል የሚጓዙ ተላላፊ መንገደኞች ከመነሻ አገር የሚደረግላቸው የሴክዩሪቲ እርምጃ አስተማማኝ መሆኑ ሲረጋገጥ መንገደኞች እና የጉዞ እቃዎቻቸው ከፍተሻ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡”

10/ “ከአዋጁ አንቀጽ 21 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (6) እንደተሻሻለ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ (22) ተጨምሮ ከአንቀጽ 22 እስከ 25 የተቀመጡ ነባር ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸዉ ከአንቀፅ 23 እስከ 26 ሆነዉ ተሻሽለዋል፤”

“22. ስለ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አገልግሎት ክፍያ

1/ ኦፕሬተሮች እና በኤርፖርት ውስጥ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አገልግሎት የሚያገኙ ማናቸውም አካላት የሴኪዩሪቲ አገልግሎት ክፍያ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ይፈጽማሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀውን የሴኪዩሪቲ አገልግሎት ክፍያ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተመራጭ ሃሳቦችን ተከትሎ ከራሱ መንገደኞች፣ከሌሎች ኦፕሬተሮች እና በኤርፖርት ውስጥ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አገልግሎት ከሚያገኙ ማናቸውም አካላት በመሰብሰብ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ገቢ ያደርጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀውን የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ አገልግሎት የክፍያ ተመን የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተመራጭ ሃሳቦችን ተከትሎ በየጊዜው እየተጠና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ በጋራ ይወሰናል፤ይሻሻላል፡፡”

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) የተመለከተውን የክፍያ ተመን የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ባለው ተቋማዊ አሰራር መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ---- ቀን /2018 ዓ.ም

ታዬ ዐጽቀስላሴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት